ታሕሳስ 2004 ዓ.ም

# <u>ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ” ሲዳሰስ</u>

## ክፍል አራት

## <u>ኢሮቦችና የዳር ድንበር ጥያቄ፣</u>

**ከበየነ ገብራይ**

ዘይተቐልዐ ታሪክ ህዝቢ ኢሮብ (ያልተገለጠ የኢሮብ ህዝብ ታሪክ) በሚል ርእስ በተዘጋጀው ዶኩመንታሪ ፍልም ውስጥ <u>ኢሮበቶት ኣብ ምክልኻል ዓዲ</u> (ኢሮቦችና የዳር ድነበር ጥያቄ) በሚለው ንኡስ ርእስ ስር የሚተረከው ወደ 12 ደቂቃ የሚወሰደውን አጭር ትረካ ልብ ብሎ ያዳመጠ ሰው፣

- o ከጥንት ከጠዋቱ በአፈታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍልን የመጣው የኢሮብ ህዝብ ዳር ድንበሩ ሲነካ ቀፎው እንደተነካበት ንብ በአንድነት በመነሳት እንዴት ዳር ድንበሩን ይከላከል እንደነበረ ሲተረክ፣
- o የገጂዎችን ክህድትና ድክምትን ለመሸፋፈን ሲባል እርስ በርስ የሚጋጩ ሃሳቦች ሲቀርቡ፣
- o መንግስትን ለማስደሰት ሲባል መንግስት ያላደረገውን አደረገ፣ ያላለውን አለ ሲባል፤
- o የኢሮብ ህዝብ ብቻውን የተጋፈጠው የመጀመሪያ ወረራና የሶስት ቀን ውግያን ከሁለት ዓመት በኋላ በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ከተደረገው ውግያ ጋር ለማያያዝ ሲሞከር በዚህ አጭር ትረካ ውስጥ አንድ ላይ ተደበላልቀው ሲተረኩ በግልጽ ለማዳመጥና ለማየት ይችላል።

ስለሆነም በግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. ሻዕቢያ የኢሮብ ወረዳን በወረረበት ወቅት በኢሮብ ህዝብ ላይ የፈጸመው ዘግናኝ ግፍ ሳይዛባ መተረክ አለበት የሚሉ፣ በግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. በተደረገው የሻዕቢያ ወረራ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት ሚና ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ምን እንደነበረ በትክክል መቀመጥ አለበት ብለው የሚያምኑ ኢትዮጵያዊያን ሁሉና በተለይ ደግሞ የኢሮብ ህዝብ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከታቸው የኢሮብ ምሁራን በዶክመንታሪ ፍልሙ <u>ኢሮበቶት ኣብ ምክልኻል ዓዲ</u> በሚል ንኡስ ርእስ ስር የሚተረከውን አጭር ትረካ መለስ ብለው ልብ ብለው ደግሞ ደጋግሞ እንዲያዳምጡትና የራሳቸው ግምገማ እንዲያደርጉበት ለማሳሰብ እወዳለሁ።በበኩሌም ይህ ፈጽሞ በዝምታ መታለፍ የለበትም ከሚል ጽኑ እምነት በመነሳት በዚህ ንኡስ ርእስ ስር በሚተረከው አጭር ትረካ ላይ ያለኝ አስተያየት ለውይይት በአራት ንኡሳን ክፍሎች በመክፈል እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

### <u>ሀ. በትረካው ውስጥ ታሪክ ሳይዛባ የተተረከበት ክፍል ነው ያልኩት፣</u>

- ➢ ጣሊያን በ1928 ዓ.ም በሰንዓፈ በኩል የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢትዮጵያን መሬት በረገጠበት ወቅት ኢሮቦች ቆፎው እንደተነካ ንብ በአንድ ላይ በመነሳት ዳር ድንበራችን አናስነካም በማለት የጣሊያን ወራሪ ጦር እንቅስቃሴን ስለገቱት፣ የጣሊያን

ወራሪ ጦር መሪ በወቅቱ የአከባቢው ገዢ ለነበሩ ለቀማት ሲፋሪ ወልደገሪማ የተለያየ ጥቅማጥቅም በመስጠት ኢሮቦችን እንዲከፋፍሉለት ሲጠይቃቸው ብልሁ ቀማት ሲፋሪ ወልደገሪማ ኢሮቦችን በምስር በማስመሰል፣ <u>ኢሮብ ቢርሲን ኪኒ (ኢሮቦች ምስር ናቸው)</u> በማለት ኢሮቦችን በዳር ድንበራቸው ጥያቄ ለመከፋፈል እንደማይቻል በቅኔያዊ አነጋገር የመለሱለትን መልስ ዶኩመንታሪ ፍልም የታሪኩን አዋቂ በመጥቀስ በጥሩ ቋንቋ አሰቀምጦታል።

- ከ14 ዓመት በፊት በግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. ሻዕቢያ በሞኖክሶይቶና በሰንዓፌ በኩል የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢትዮጵያን መሬት በወረረበት ወቅትም የኢሮብ ህዝብ ማንም ረዳት ሳይጠብቅ ዳር ድንበሩን ለመጠበቅ በአንድነት በመነሳት ከሻዕቢያው ወራሪ ጦር ጋር ለሶስት ቀናት ለብቻው እንደተዋደቀ ዶኩመንታሪ ፊልሙ በምስልና በድምጽ በማስደገፍ ስሜትን በሚቀሰቅስ አቀራረብ ባጭሩም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ተርኮታል።
- ምንም እንኳን ዛሬ በአቶ መለስ ዜናዊና መሰሎቻቸው አንድ ሶስተኛው የኢሮብ መሬት ለሻዕቢያ የተሰጠ ቢሆንም፣ (ለተጨማሪ መረጃ WWW.irobmablo.org ላይ No one is intitled to infringe on the unity of the Irob people በሚል ርእስ በኢ..መ.ተ.ማ. የተሰራጨውን መግለጫ ይመልከቱ፥) ዶኩመንታሪ ፍልሙ የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት የኢትዮጵያ መሬት ለአንድም ቀን እንኳን ዛሬ ኤሪትርያ ተብሎ ከሚታወቀው ክልል ጋር ሆኖ እንደማያውቅ በማያሻማ ቋንቋ በግልጽ አሰቀምጦታል።
- በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው አገዛዝ ሻዕቢያ በድንገት ምንም ሳይታወቅ ወረረን በማለት ዓይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ ሊለን ቢሞክርም፣ ዶኩመንታሪ ፊልሙ ሻዕቢያ ግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. የኢሮብ መሬትን በይፋ ከመውረሩ በፊት በሚያዝያ 28 ቀን 1990 ዓ.ም. የኢሮብ መሬትን በተለይ ዓውዳ፣ ዋርዓትለና ዓይጋ የመሳሰሉ ገዢ መሬቶችን በሄሊከፕተር እየተዘዋወረ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዳሰባሰበ፣ ሰራዊቱን በመከታ፣ አይሃ፣ ማይጺዓና በሞኖክሶይቶ በኩል ከአንድ ወር በፊት ጀምሮ እያሰባሰበና እያዘጋጀ እንደሰነበተ በግልጽ ቋንቋ አስቀምጧል።
- በሚገባ ታጥቆ፣ በሻለቆች ደረጃ ተደራጅቶ የኢሮብ መሬትን ግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. የወረረው የሻዕቢያን ሰራዊት የኢሮብ ህዝብ ያለማንም ረዳት ለብቻው ለ3 ቀን ያህል የተዋጋው 50 የሚሆኑ ሚሊሽያዎች የታጠቁትን ቀላል መሳሪያ ብቻ በመያዝ አንዱ ባለ-ነፍጥ ሲወድቅ የቀረው ያ የወደቀው ምሊሻን ብረት በማንሳት እንደነበረ ዶኩመንታሪ ፍልሙ በግልጽ ቋንቋ አስቀምጦታል።
- እስከዛሬ ድረስ በአቶ መለስ ዜናዊ በሚመራው የኢትዮጵያ መንግስት በሻዕቢያ ለመጠለፋቸው ዕውቅና የነፈጋቸው ንጹሃን የኢሮብ አርሶ አደሮች ወደ 108 የሚሆኑ በሻዕቢያ የተወሰዱ የኢሮብ ዜጎች በሚል ዶኩመንታሪ ፍልሙ እነዚህ ንጹሃን ዜጎቻችን በሻብያ ተጠልፈው ከተወሰዱበት ጀምሮ እስከዛሬ መዳረሻቸው ሆነ ህልውናቸው ምንም እንደማይታወቅ በግልጽ ቋንቋ አስቀምጧል።

ለዚህም በበኩሌ ለዶኩመንታሪ ፍልም አዘጋገሮች አመሰግናቸዋለሁ።

<u>ለ. በትረካው ውስጥ የገዢዎችን ክህደት ለመሸፈን ሲባል እርስ በርሱ የሚጋጭ/የሚቃረን አባባል የሚተረክበት ክፍልም አለ፣</u>

*የዶኩመንታሪ ፊልሙ አዘጋጆች በትክክለኛ ታሪክና የድርጅት ወይም የመንግስት ፕሮፓጋንዳ መካከል ያለውን ልዩነት ይጠፋቸዋል የሚል ግምት የለኝም። ሆኖም ግን የዶኩመንታሪ ፊልሙ አዘጋጆች በፊልሙ በተለያዩ ክፍሎች እንዳደረጉት ሁሉ በዚህም እውነተኛውን ታሪክንና የህወሓት አመራር ፕሮፓዳንዳን አንደተለመደው አንድ ላይ እያደባለቁ ይተርኩልናል፣ አንዳንዴም በሬ ወለደ ዓይንት የገዢዎች ውሸት እንደ ሃቀኛ ታሪክ አስመስለው እንደገዢዎቹ ሊግቱን ሞክረዋል።ለምሳሌ 1990 ዓ.ም. ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመው ወረራን በተመለከተ አቶ መለስና መሰሎቻቸው እንደሚሉን የኢትዮጵያ መንግስት ሻዕቢያ ኢትዮጵያን ለመውረር ዝግጅት እያደረገ እንደነበረ መንግስት ምንም እውቀት አልነበረውም የሚለውን አባባል የዶኩመንታሪ ፍልም አዘጋጆችም ለአድማጮቻቸው ለማሳመን እንደሚከተለው ሊሉን ሞክረዋል።እጠቅሳለሁ፣*

- ***<u>"መንግስትን ህዝብን ንድኽነት ንሓንሳብን ንዘለዓለምን ካብ እንግድዓኡ ንምውጋድ ናይ ልምዓት አንፈት ተሊሙ ሀርኮትኮት እናበለ እንተሎ ሃንደበታዊ ጸላኢ ገጢሙዎ"</u>***

*ትርጉም፣ <u>መንግስትና ህዝብ ድህነትን ላንዴና ለሁሌ ከጫንቃቸው ለማስወገድ የልማት ዕቅድን በማውጣት ደፋ ቃና እያለ እንዳለ ያልታሰበ ድንገተኛ ጠላት ገጠማቸው</u>*

*ዶኩመንታሪ ፍልም አዘጋገሮች ከላይ የተቀመጠውን ዘንግተው ነው መሰለኝ ከዚህ አባባላቸው ጋር በቀጥታ የሚላተም የሻዕቢያ ዝግጅት መኖሩን እንኳን መንግስት ብዙ የስለላ መዋቅር ያለው ይቅርና ተራ ሰውም ሊያወቅ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን በግልጽ የሚያሳይ አባባል በሰኮንዶች ልዩነት ውስጥ እንዲህ በማለት ያስደምጡናል። እጠቅሳለሁ*

- ***<u>"ሻዕቢያ ቅድሚ ዕላዊ ወራር ምፍጻሙ 28 ሚያዚያ 1990 ዓ.ም. እንዳልገዳ፣ ዓወዳን ወርዓትለን ቢህሊከፐትራት ከዘንቢ ወዓለ። ወርሒ እኳ አይመልአን ብመከታ፣ አይሃ፣ ሞኖክሶይቶን ማጭዓን እውን አጋር ሰራዊቱ ምጽጋዕ ጀመረ። እቲ ኩናት ድማ ብ23 ግንቦት 1990 ዓ.ም. ተጀመረ"።</u>***

*ትርጉም፣*

- *<u>ሻዕቢያ መደበኛ ወረራ ከመፈጸሙ በፊት ሚያዝያ 28 ቀን 1990 ዓ.ም. እንዳልገዳ. ዓውዳና ወርዓትለን የመሳሰሉ ቦታዎች በሂሊኮፕተር ሲሰልል ዋለ። ወር እንኳን አልሞላም በመከታ፣ አይሃ፣ ሞኖክሶይቶና ማይጪዓ በኩል እግረኛ ሰራዊቱን ማስጠጋት ጀመረ። ውግያው ደግሞ በግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. ተጀመረ።</u>*

*ውድ አንባቢዎች፣ ዶኩመንታሪ ፊልሙ በሰኮንዶች ልዮነት ውስጥ ከሚያቀርባቸው ከላይ ከተቀመጡ ሁለት እርስ በርስ የሚጋጩ/የሚቃረኑ አባባሎች ሃቀኛው የተኛው ነው? ለጊዜው ፍርዱንና መልሱን ለናንተው ለአንባቢያን ልተወው።*

***<u>ሐ. ገጂዎችን ለማስደሰትና ለመወደስ ሲባል ያልተደረገው እንደተደረገ፣ ያልተባለው እንደተባለ ተደርጎ የተተረከበት ክፍልም አለ።</u>***

ዶኩመንታሪ ፊልሙ አሁን በስልጣን ላይ ያለውን በአቶ መለስ የሚመራውን የህወሓት መሪዎችና ካድሬዎቻቸው ክህደትና ድክመትን ለመሸፈን ሲል ያልተባለው እንደተባለ፣ ያልተደረገው እንደተደገ በማስመሰል እንደሚከተለው ሊያስደምጠን ሞክረዋል፣ እጠቅሳለሁ፣

- ✓ **"ድሕሪ ናይ ሰለስተ መዓልቲ ተቀጻጸልቲ ውግኣት ግና መንግስቲ ህዝቢ ከይሃልቕ ካብቲ ኩናት ከንሳሕብ ከምዘለዎ ብዘውረዶ መምረሒ መሰረት ህዝቢ አንሳሒቡ።**
- ✓ **ካብ ሰገር ሩባ ዓሊተና ንምዕራብ ገጽ ዘሎ መረት ኢሮብ ሻዕቢያ ተቆጻጸሮ።**
- ✓ **አብዚ ጊዘ ብርኪ አጥሪዮም ክሃድሙ ዘይከአሉ ህጻናትን ሽማግለታትን ግዳይ እቲ ግፍዒ ኮይኖም።**
- ✓ **ከባቢ 108 ዝኩኑ ኢሮበቶት ብሻዕቢያ ተወሲዶም አበይ ከምዝአተዉ አይፍለጥን።**
- ✓ **ሻዕቢያ ንመረት ኢሮብ ንክልተ ዓመት ዝአክል ብምቁጽጻር ንብረትን መረበትን ኢሮበቶት እናበሳበሰ ጸንሐ"**

ትርጉም፣

- ✓ *ከሶስት ቀን ተከታታይ ውግያ በኋላ መንግስት ህዝቡ እንዳያልቅ በማሰብ ከውግያው እንዲያፈገፍግ ባወረደው መመሪያ መሰረት ህዝቡ አፈገፈገ።*
- ✓ *ከዓሊተና ወንዝ ወደ ምዕራብ በኩል ያለው የኢሮብ መሬት ሻዕቢያ ተቆጣጠረው*
- ✓ *በዚህ በወረራው ወቅት ጉልበት አግኝተው ለመሸሽ ያልቻሉ አረጋዊያንና ህጻናት የሻዕቢያ ግፍ ሰለባ ሆኑ።*
- ✓ *ወደ 108 የሚሆኑ ኢሮቦች በሻዕቢያ ተወስደው የት እንደደረሱ እስካሁን አይታወቅም።*
- ✓ *ሻዕቢያ የኢሮብን መሬት ለሁለት ዓመታት ያህል ጊዜ በመቆጣጠር የኢሮቦች ንብረትና መኖሪያ ቤቶቻቸውን ሲዘርፍና ሲያበሳብስ ቆየ።*

አጠቃላይ ኢሮበቶት አብ ምክልካል ዓዲ በሚል ርእስ የሚተረከው አጭር ትረካ ሆነ እያንዳንዳቸው ከላይ የተቀመጡ ዓረፍተ-ነገሮች ራሳቸውን ችለው ሰፋፊ መጣጥፎች ሆነ መጻህፍት ሊጻፍባቸው የሚችሉና የሚገቡም ናቸው። ሆኖም ግን ለጊዜው የራሴን ሃሳብና ትችት ለይደር በማሳደር ለምናደርገው ውይይትና ለወደፊቱ ለሚጻፉ መጣጥፎች ሆነ መጽሀፍ/ጻህፍት ለመጻፍ ለሚፈልጉ እንደ መነሻ ሊረዱ ይችላሉ የምላቸውን ጥያቄዎች ብቻ አንስቼ ልለፍ፣

1. ግንቦት 23 ቀን 1990 ዓ.ም. ሻዕቢያ የኢሮብ ወረዳን በይፋ ከመውረሩ በፊት እውነት የኢትዮጵያ መንግስት ሻዕቢያ አከባቢውን እንደሚወር ምንም መረጃ አልነበረውም?
2. ወረራው ከተጀመረ በኋላ የኢሮብ ህዝብ ብቻውን ሻዕቢያን ለሶስት ቀን ተጋፍጦ ሲዋደቅ የኢትዮጵያ መንግስት ለምን ረዳት ኃይል ለመላክ አልቻለም/አልፈለገም?
3. ከዓሊተና ወንዝ ወደ ምዕራብ በኩል ያለው የኢሮብ መሬት በሻዕቢያ ሰራዊት ቁጥጥር ስር ሲወድቅ የሻዕቢያ ሰራዊት አሰቃቂ ግፍ ቀማሽ የሆኑት ዶኩመንታሪ ፍልሙ እንደሚለን ለመሸሽ ያልቻሉት ህጻናትና ሽማግሌዎች ብቻ ናቸው ወይስ አጠቃላይ ህዝቡ?
4. ወደ 108 የሚሆኑ ንጹሃን አርሶአደሮች በሻዕቢያ ተጠልፈው ተወስደው አድራሳቸው እስከዛሬ ድረስ እንደማይታወቅ ዶኩመንታሪ ፍልሙ በግልጽ ቢያስቀምጥም ለምን

እነዚ ንጹሃን አርሶ አደሮች በራሳቸው መንግስት በሻዕቢያ እንደተጠለፉ ዜጎች እውቅና እንደተነፈጋቸው ሊጠይቅ አልቻለም/አልፈለገም። ለምን?

5. በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢትዮጵያ አገዛዝ ለነዚህ በሻዕቢያ ተጠልፈው እስካሁን መዳረሻቸው ለማይታወቁ ከ100 በላይ ንጹሃን ዜጎች በሻዕቢያ እንደተጠለፉ ዜጎቹ እውቅና በመስጠት ለምን ለማስፈታት ጥረት ለማድረግ አልቻለም/አልፈለገም?
6. ሻዕቢያ ከዓሊተና ወደ ምዕራብ ያለው የኢሮብ መሬትን ለመቆጣጠር ባካሄደው የ3 ቀን ውግያ በርካት የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት ውድ ህይወታቸውን ለዳር ድንበራቸው ገብረዋል። እነዚህ ለዳር ድንበራቸው ሲሉ ውድ ህይወታቸውን የከፈሉ ጀግኖች ስንት ናቸው? እንማን ናቸው? ማን የት ቦታላይ ነው የወደቀው? ለምን የነዚህ ጀግኖች ስም ዝርዝር በዶኩመንታሪ ፍልም ለመገለጽ ያልተቻለው/ያልተፈለገው?
7. ሻዕቢያ ከዓሊትና ወደ ምዕራብ በኩል ያለውን የኢሮብ መሬት ለሁለት ዓመት ያህል ተቆጣጥሮ በቆየበት ጊዜ በተቋማትና በግለሰብ ነዋሪዎች ንብረት ያደረሰው ውድመትና ዝርፊያ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም ግን በትክክል ሻዕቢያ ያወደማቸው ተቋማት ብዛትና የደረሰው ውድመት፣ ከግለሰብ ነዋሪዎች የተዘረፈው ንብረት ዓይነትና ብዛት፣ ….ወዘተ. በተመለከተ በዶኩመንታሪ ፊልም የቀረበ መረጃ የለም። ለምን ዶኩመንታሪ ፊልም እነዚህን መረጃዎች ለማቅረብ አልቻለም/አልፈለገም? ……..ወዘተ.

እንደኔ እምነት የሻዕቢያ የ1990 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ወረራና የኢሮብ ህዝብ በሻዕቢያ ቁጥጥር ስር የቆየበት ሁለት ዓመትን በተመለከተ ገና ገሃድ ያልወጡ የተደበቁ በርካታ መዳሰስ ያለባቸው እነታዎች ስላሉ የኢሮብ ህዝብ ቁስል ይሰማናል የምንል ወገኖች ሁላችን በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በጋራ በመስራት ትክክለኛ ታሪክ በመጻፍ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ መቻል ይኖርብናል። ስለሆነም ውይይቱን ቢያንስ ከላይ በቀረቡ ጥያቄዎች ዙሪያ በመጀመር ስራውን ካሁኑኑ መጀመር መቻል አለብን እላለሁ። ይህ ስራ በትክክል እንዲሰራ ከፈልግን ደግሞ ይህ የ1990 ዓ.ም. የሻዕቢያ ወረራን የሚመለከቱ መረጃዎችና ዶኩመንቶች የሚሰባሰቡበትና ለታሪክ ጸሃፊዎች የሚከማቹበት አንድ ማእከል ባስቸኳይ መመስረት መቻል አለበት። ይህ ማእከል ለወደፊቱ በጋራ ስምምነት እስከሚመሰረት ድረስ ደግሞ ለጊዜው የኢሮብ ማብሎ ድረ_ገጽን በጊዚያዊነት በመጠቀም ሁሉም ይህን ጉዳይ የሚመለከቱ መረጃዎች ሆኑ ዶኩመንቶች፤ ወደ ድረ_ገጹ ቢላኩና ቢሰባሰቡ መልካም ነው እላለሁ።

<u>መ. የኢሮብ ህዝብ ዛሬ የሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል?</u>

- <u>ኢሮበቶት አብ ምክልኻል ዓዲ</u> በሚል ንኡስ ርእስ ስር የሚተረከው የ12 ደቂቃ የዶኩመንታሪ ፍልም ትረካ ውስጥ በቁመንነገሮችና ትክክለኛ የታሪክ ክንዋኔዎች መካከል የህወሓት መሪዎች ውሸትና ፕሮፓጋንዳም እየተቀላቀለ መቅረቡ ፊልሙ አሁን በዚህ መልክ እንዲዘጋጅ የተፈለገበት መሰረታዊ ዓላማ የኢሮብ ህዝብ ታሪክን ከህወሓት ታሪክ ጋር ለማያያዝ እንደሆነ በዚህ ክፍል በሚቀርበው ትረካ በገሃድ ይታያል። የፊልሙ ዓላማ ይህ ሆኖ ሳለ የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት ይህን በዶኩመንታሪ ፊልሙ የሚተረከውን ሃቁን ከውሸትና ከህወሓት አመራር ፕሮፓጋንዳ ጋር ቀላቅሎ እንደ ኢሮብ ህዝብ ታሪክ አድርጎ ሲያቀርብልን እየሰማን እንዳልሰማን፣ እያየን

እንዳላየን ሆነን፣ በፍርሃት ተሸብበን ታሪካችን ሲበረዝ ዝምታን በመረጥንበት አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ እንገኛል።

- በ1990 ዓ.ም. ሻዕቢያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በአቶ መለስ ዜናዊና መሰሎቻቸው በህዝባችንና በሀገራችን የተፈጸመውን ክህደት እያዩና እያዳመጡ እንዳላዩና እንዳልሰሙ ሆኖ ማለፍ ነገ በታሪክ የሚያስጠይቅ አሳፋሪ ድርጊት መሆኑ ብዙዎቻችን የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት፣ በተለይ የተማርን ነን የምንል ወገኖች ዛሬ የዘነጋንበት ሁኔታ ላይ ነን ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም።አቶ መለስ ዜናዊ የሚመሩት ድርጅታቸው ህወሓት ሆነ መንግስታቸው ነገ ሃላፊዎች መሆናቸው፣ የኢሮብ ህዝብና የሚኖርበት መሬቱ ግን ዘለዓለማዊ መሆናቸው የዘነጋንበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል። የኛ ትውልድ አባቶቻችን ጎበዝ አባት ሰነፍ ልጅ ሲወልድ የሚመስሉት <u>ጊራ ጎምቦድ ዳልታ</u> (እሳት አመድ ይወልዳል) የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የኛውን ትውልድ የሚወክል ይመስለኛል።
- የአሮብ ህዝብ በማንነቱና በውስጥ ጉዳዩ ማንንም ጣልቃ ሳያስገባ የራሱ ጉዳይ ራሱ ብቻ ሲፈጽም የነበረበት የትናንቱ የአባቶቻችን ትውልድ የነበረው ውህደትና አንድነት ዛሬ በዘመነ ህወሓት በኛ ትውልድ መካከል የለም ብል አልተሳሳትኩም። ህወሓት እንደ ድርጅት የኢሮብ ህዝብን ከማናቸው ካሁን በፊት ከነበሩት አገዛዞች የበለጠ ለመከፋፈልና እርስ በርሳችን እንድንባላ ለማስደረግ ችሏል ብል ያጋነንኩ አይመስለኝም። አባቶቻችን አንድነቱን አሰጠብቀው እስከ ዛሬ በኢሮብነቱ አንድላይ ያቆዩት ህዝባችን በኛው ዕድሜ፣ በዘመነ ህወሓት እርስ በርሱ እየተባላ ነው፣ ከህወሓት ካድሬዎቻቸውና ደጋፊዎች ውጭ ያለው ህዝባችን ሆነ ከህወሓት ፖለቲካዊ አመለካከት የተለየ ፖለቲካዊ አመለካከት ያለቸው ወገኖች በፍርሃት ቆፈን ተሸብበው ራሳቸውን አጎንብሰው እንዲኖሩ የተገደዱበት ሁኔታ ውስጥ ነን።
- የኢሮብ ህዝብ የሚኖርበት አዶሓ ኢሮብ በሚል የሚታወቀው መሬታችን ለአንዲት ደቂቃም እንኳን ቢሆን ዛሬ ኤሪትርያ ተብሎ በሚታወቀው ክልል ስር ሆኖ እንደማያውቅ በግልጽ ቢታወቅም፣ በአቶ መለስ ዜናዊ በጎ ፍቃድ ከአንድ ሶስተኛው በላይ የሆነው የኢሮብ ህዝብ መኖሪያ የሆነው መሬታችን ለሻዕቢያ ተሰጥቷል። ይህ የተሰጠው መሬት ስፋት ከነዝርዝር የመንደሮች ስምና በካርታ ጋር በማስደገፍ ኢ.መ.ተ.ማ. (የኢሮብ ህዝብ መብት ተሟጋች ማህበር) ለሁሉም ኢሮቦች በግልጽ በማሳየት ኢሮቦች በአንድነት ለአቶ መለስ ዜናዊና መንግስታቸው ይህ ህገወጥ ውሳኔያቸውን በይፋ እንዲሰርዙ በጋራ እንጠይቅ ብሎ ያቀረበው ጥሪ እንደተለመደው በዝምታ የሚታለፍበት ሁኔታ ላይ ነን።
- ከ100 በላይ የሚሆኑ ንጹሃን ወገኖቻችን በ1990 ዓ.ም ወረራ ወቅትና አከባቢው በኤርትራ ቊጥጥር ሥር በነበረበት ሁለት ዓመታት ግዜ በሻዕቢያ ተጠልፈው ተወስደው እስከዛሬ መዳረሻቸው ሆነ ህልውናቸው በማይታወቅበት ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም እንደ ብሄረሰብ በኢትዮጵያ መንግስትም ሆነ በዓለምአቀፍ ማህበረሰብ ላይ እነዚህ ወገኖቻችን በማስፈታት ሆነ መዳረሻቸውን ለማወቅ በሚደረገው ትግል በጋራ ለመስራት በማንችልበት በተበታተነ ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። ይባስ ብሎም አንዳንድ ወገኖች ይህ የኢሮቦች ለመብታቸው በጋራ ለመከራከር መሰባሰብ ተግባራዊ እንዳይሆን የሚፈልገው የህወሓት መንግስት አፈቀላጤዎች በመሆን በተለያየ ሰበብ አስባብ ለመሰባሰብ

የሚደረጉትን ሙከራዎች ለመከፋፈልና ለማስፈራራትም እየሞከሩ ያሉበት ሁኔታ ውስጥ ነን።

- በአከባቢው በሰፈነው ድርቅ፣ የእርሻ መሬት እጦት፣ የስራ እጦት ምክንያት፣ እንዲሁም ባለው ስርዓት ብልሹነት ተማረው በርካታ ወጣቶቻችን ወደየ አቅጣጫው በስደት እየተበታተኑና እየጠፉ ባሉበት፣ ሽማግሌዎቻችን ደግሞ አከባቢውን ለቀው እየፈለሱ ያሉበት ሁኔታ ውስጥ ነን።.........ወዘተ.

<u>ከዚህ ቀውጢ ሁኔታ ለመውጣት ምን ማድረግ አለብን?</u>

ዛሬ የኢሮብ ብሄረሰብ እንደ ብሄረሰብ የመቀጠል ዕድሉ ከምን ጊዜም በላይ አደጋ ውስጥ የገባበት ወቅት ላይ ነን ቢባል ስህተት አይደለም። ከዚህ ቀውጢ ሁኔታ ለመውጣት የምንችለው ደግሞ ሁሉም የብሄረሰቡ አባላት ያለምንም ቅድመሁኔታ ሊያሳትፍ የሚችል መድረክ በመፍጠር በግልጽ በችግሮቻችን ላይ ለመወያየት ስንችል ብቻ ነው። ስለሆነም አንድንም ወገን የማያገል፣ ሁላችን የብሄረሰቡ አባላት ያለምንም መሸማቀቅና ፍርሃት ልንሳተፍበት የምንችል በአባቶቻችን አጠራር <u>አዶሓ ኢሮቢህ አግለ</u> (አጠቃላይ የኢሮቦች ተወካዮች ሊገኙበት የሚችሉ ጉባኤ) ማዘጋጀት ያስፈልገናል። በርግጥ ዛሬ እንደዚህ በተለያየ ክፍለዓለማት፣ በሀገር ደረጃም በተለያዩ ከተሞች ተበታትነን ባለንበት ሁኔታ ይህ የተባለው ሁሉንም የሚያሳትፍ ጉባኤ ማዘጋጀትና ማካሄድ እንደሚከብድ ግልጽ ነው። ሆኖም ግን ከልብ ከታዘነ እንባ አይገድም ነውና፣ ሁላችን ለዚህ ጉባኤ ዝግጅት መረባረብ መቻል አለብን። ይህን የሁሉንም አሳታፊ ጉባኤ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በመጀመሪያ በየአከባቢው በቀላሉ በአካል ለመገናኘት የምንችል በአካል በመገናኘት መመካከር መጀመር መቻል አለብን። ከዚህ በተጨማሪም ዘመን አመጣሹን ተክኖሎጂን መጠቀም የምንችል ወገኖች ከያለንበት በመገናኘት በጉዳዩ ላይ መወያየት መቻል አለብን።ይህ ሁሉን አሳታፊ ጉባኤ ተግባራዊ እንዲሆንና በዚህ ጉባኤም አንድ ስምምነት ላይ በመድረስ ህዝባችንን ለመታደግ ከልብ ከፈለገን እያንዳንዳችን የሚከተሉትን ቅደመ ሁኔታዎችን ለማሟላት ጥረት ማድረግ መቻል አለብን።

- ከጥላቻ በመራቅ በመሰረታዊ የጋራ ጉዳያችን ላይ ብቻ ማተኮር
- ከፍርሃት በመላቀቅ ለሃቅ፣ ለህዝብ መብተና ለዳር ድንበራችን መከበር፣ መከፈል ያለበትን መስዋዕትንት ለመክፈል መዘጋጀት፣
- ከግል ጊዜያዊ ጥቅምና ፍላጎት በፊት የህዝብና የሀገርን ጥቅም ማስቀደም፣
- መደማመጥ፣ ያሉትን ልዩነቶች በሜዋ ቋንቋ መወያየትን፣ በሃሳብ አቅራቢው/ዋ ማንነት ላይ ሳይሆን በሚያቀርበው/በምታቀርበው ሃሳብ ላይ ማተኩርን መልመድ ፣
- በሚያለያዩን ሃሳቦች በጨዋ ቋንቋ ውይይቱን እየቀጠልን በኢሮብነታችን ብቻ ሊያስማሙን በሚችሉ፣ ለምሳሌ የድንበር ጥያቄና በሻዕቢያ የተጠለፉ ወገኖቻችን ጉዳይ በተመለከተ በአንድነት ለመስራት መጀመር መቻል አለብን።.......ወዘተ.

በሚቀጥለው መጣጥፌ እስከምንገናኝ በያላችሁበት በቸር ሰንብቱ

ከኔ ጋር ለሚደረግ ግኑኝነት <u>beyene54@yahoo.com</u> መጠቀም ይቻላል።